በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት
ኤጀንሲ

THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN INVESTMENT
AGENCY

ቀን 28 የካቲት 2003
DATE

ቁጥር ኢኢኤ/ኢጠ3/007
REF.No.

ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>የተሻሻለው የተሽከርካሪ ማበረታቻ መመሪያን ይመለከታል</u>

ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ መመሪያ መውጣቱ ይታወሳል፡፡

ይህንን መመሪያ ማሻሻል በማስፈለጉ በመመሪያው አንቀፅ 15 መሠረት ቦርዱ ዓርብ የካቲት 18 ቀን 2003 ዓ.ም ባደረገው ሰማንያ ዘጠነኛ ስብሰባ ያፀደቀውን የተሻሻለ የተሽከርካሪ ማበረታቻ መመሪያ አያይዘን እየላክን መመሪያው ከየካቲት 18 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል አስታውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

መኮንን ማንያዘዋል
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ
ሰብሳቢ

ግልባጭ፡

- ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ

  <u>አዲስ አበባ</u>

ስልክ 011- 551 00 33
Tel. 011-553 72 86

✉ 2313
Website = WWW. ethioinvest.org
E-mail address = ethiopian.invest@ethioinvest.org

ፋክስ
Fax; 011-551 43 96

## *ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን እንደገና ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ*

እንደ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ዓይነትና ባሕሪ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ እንደሚወሰን በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 84/1995 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 9 የተደነገገ ስለሆነ፤

በዚህም መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው ስለሚገቡ ተሽከርካሪዎች አፈቃቀድ ቦርዱ በ1999 ዓ.ም. እንደገና የተሻሻለ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ያደረገ በመሆኑ፤

ቀደም ሲል ለአስጎብኚነት ሥራ እና ለመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ (ICT) ልማት በተናጠል ወጥተው በነበሩ መመሪያዎች የሚሰጡ የተሽከርካሪ ማበረታቻዎችን በአንድ ላይ አጠቃሎ ማውጣት በማስፈለጉ፤

ኢንቨስትመንትን ይበልጥ ለማበረታታት እና ለማስፋፋት ተሽከርካሪዎች ያለ ጉምሩክ ቀረጥ ከውጭ እንዲገቡ የሚፈቀዱባቸውን ሁኔታዎች እንደገና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994 (እንደተሻሻለ) እና በደንብ ቁጥር 84/1995 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 9 መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል I - ጠቅላላ

### አንቀጽ 1

### አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ "ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እንደገና ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 3/2003 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2

### ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ፦

1) ‹‹ተሽከርካሪ›› የሚለው ቃል የደረቅ፣ የፍሳሽ/የዝቃጭ ወይም ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪናን፣ ሞተር ብስክሌትን ፣ ፒክ-አፕን፣ ስቴሽን ዋገንን፣ ቶም ካርን፣ የሠራተኛ ማጓጓዣ አውቶቡስን፣ ሚኒባስን፣ ጀልባን እና ዴሊቨሪ ቫንን ብቻ የሚያካትት ነው፡፡

2) ‹‹አውቶቡስ›› ማለት ቢያንስ 45 (አርባ አምስት) መቀመጫ ያለው የሰው ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ነው፡፡

3) ‹‹ሚኒባስ›› ማለት ከ10 (አሥር) ያላነሰ እና ከ12 (አሥራ ሁለት) ያልበለጠ መቀመጫ ያለው የሰው ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ነው፡፡

4) ‹‹ፒክአፕ›› ማለት 2WD ወይም 4WD የሆነ፣ የሲሊንደሩ ብዛት 4 (አራት) እና የመጫን አቅሙ ከ700 ኪ.ግ. (ሰባት መቶ ኪሎ ግራም) እስከ 1000 ኪ.ግ. (አንድ ሺህ ኪሎ ግራም) የሆነ ተሽከርካሪ ነው፡፡

5) ‹‹ዴሊቨሪ ቫን›› ማለት ጭነት የመጫን አቅሙ ከ3500 ኪ.ግ. (ሦስት ሺህ አምስት መቶ ኪሎ ግራም) እስከ 5000 ኪ.ግ. (አምስት ሺህ ኪሎ ግራም) የሆነ ሽፍን ተሽከርካሪ ነው፡፡

6) ‹‹የጭነት መኪና›› ማለት የመጫን አቅሙ ከ5000 ኪ.ግ. (አምስት ሺህ ኪሎ ግራም) እስከ 15000 ኪ.ግ. (አሥራ አምስት ሺህ ኪሎ ግራም) የሆነ ተሽከርካሪ ነው፡፡

7) ‹‹ሆቴል››፣ ‹‹ሎጅ››፣ ‹‹ሬስቶራንት››፣ እና ‹‹ሞቴል ›› በቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ደረጃ ምደባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 173/2002 መሠረት የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

8) ‹‹ሪሶርት ሆቴል›› ማለት ለመዝናናት፣ የዕረፍት ጊዜን ለማሳለፍ፣ ወዘተ. በሚያስችል መልኩ ከከተማ ራቅ ብሎ መስህብ ባለው አካባቢ የሚቋቋም ዘመናዊ ሆቴል ነው፡፡

9) ‹‹የኢንዱስትሪ ዞን›› ማለት የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች እና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲቋቋሙበት ከከተማ ወጣ ብሎ የተከለለ ቦታ ነው፡፡

10) "ደንብ" ማለት ስለ ኢንቨስትመንት ማበረታቻና ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 84/1995 (እንደተሻሻለ) ነው፡፡

## <u>ክፍል II</u>

## <u>ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድላቸው የኢንቨስትመንት መስኮችና የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት</u>

### <u>አንቀጽ 3</u>

### <u>ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የማስገባት ማበረታቻ የሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት መስኮች</u>

በዚህ መመሪያ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የማስገባት ማበረታቻ የሚሰጠው ለማምረቻ ኢንዱስትሪ፤ ለግብርና፤ ለኢንዱስትሪ ዞን ግንባታ፤ ለአስጎብኝነት ሥራ፤ የኮከብ ደረጃ ላላቸው ሆቴሎች (የሪሶርት ሆቴሎችን ጨምሮ)፣ ሞቴሎች፣ ሬስቶራንቶችና ሎጆች፤ ለመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ (ICT) ልማት እና ለኮንስትራክሽን፣ ለውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ግንባታ ሥራ ተቋራጭነቶች እንዲሁም ለልዩ ሥራ ተቋራጭነት የኢንቨስትመንት መስኮች ይሆናል፡፡

# <u>አንቀጽ 4</u>

## <u>ለማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች</u>

1) በዚህ መመሪያ በአባሪው ከተመለከቱት በስተቀር ቢያንስ 25 ሚሊዮን ብር ኢንቨስት በማድረግ በማምረቻ ኢንዱስትሪ የሥራ መስክ ለሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ የሚፈቀዱለት የተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እንደተመለከተው በሥራ መስክ እና በሚቋቋምበት የልማት አካባቢ ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አግባብነት ያለው ማናቸውም የማምረቻ ኢንዱስትሪ አንድ የፍሳሽ/የዝቃጭ ማስወገጃ ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

3) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ለተመለከቱት የማምረቻ ኢንዱስትሪ የኢንቨስትመንት መስኮች ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀው ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

| ፊ.ተራ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| ሀ | <u>የምግብ ኢንዱስትሪ</u><br>1. ሥጋና የሥጋ ውጤቶችን ማቀነባበር<br>2. ዓሣና የዓሣ ውጤቶችን ማቀነባበር<br>3. ፍራፍሬ እና / ወይም አትክልት ማቀነባበር<br>4. ጥራጥሬ፣የቅባት እህል ወይም ሌላ እህል ማቀነባበር<br>5. የምግብ ዘይት ማምረት<br>6. ወተት ማቀነባበር እና/ወይም የወተት ውጤቶችን ማምረት፣<br>7. ማካሮኒ፣ፓስታ እና/ ወይም የመሳሰሉ ምግቦችን ማምረት፣<br>8. ስታርች እና የስታርች ውጤቶችን ማምረት<br>9. ስኳር ማምረት | - | አንድ<br><br>(በማጓጓዝ ሂደት ለአቧ ራ ፣ ለፀሐ ይና ለዝናብ መጋለጥ ለሌለ ባቸው ምር ቶች) | አንድ<br><br>(በዚህ ምድብ ተራ ቁጥር 1፣ 2፣ 3 እና 6 ለተመለከ ቱት ብቻ ) | አንድ<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | አንድ | ሁለት<br><br>(በማጓጓዝ ሂደት ለአቧ ራ ፣ ለፀሐ ይና ለዝናብ መጋለጥ ለሌለ ባቸው ምር ቶች) | ሦስት<br><br>(በዚህ ምድብ ተራ ቁጥር 1፣ 2፣ 3 እና 6 ለተመለከቱት ብቻ ) | ሁለት<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| | 10. ቸኮሌት፣ ከረሜላ፣ ብስኩት ወይም የመሳሰሉ ጣፋጭ ምግቦችን ማምረት፣ | - | አንድ<br><br>(በማጓጓዝ ሂደት ለአቧራ፣ ለፀ ሐይና ለዝናብ መጋለጥ ለሌለ ባቸው ምር ቶች) | - | አንድ<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | አንድ<br><br>(በማጓጓዝ ሂደት ለአቧራ፣ ለፀ ሐይና ለዝናብ መጋለጥ ለሌለ ባቸው ምር ቶች) | - | አንድ<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |

| ተ.ራ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| | 11. ሌሎች ምግቦችን (የሕጻናት ምግብ፣ ተቆልቶ የተፈጨ ቡና፣ የሚሟሟ ቡና፣ ሻይ ወይም መሰል ምግቦች) ማምረት፣<br>12.የእንሰሳት መኖ ማቀነባበር | አንድ (በተራ ቁጥር 12 ለተመለከተው ብቻ) | አንድ (በተራ ቁጥር 11 ለተመለከተው ብቻ) | - | አንድ ( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | አንድ (በተራ ቁጥር 12 ለተመለከተው ብቻ) | ሁለት (በተራ ቁጥር 11 ለተመለከተው ብቻ) | - | ሁለት ( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| ለ | <u>የመጠጥ ኢንዱስትሪ</u><br>13.የአልኮል መጠጥ ማምረት | - | አንድ | - | አንድ ( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | አንድ | አንድ | - | ሁለት ( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| | 14.የወይን ጠጅ ማምረት፣<br>15.ቢራ እና /ወይም የቢራ ብቅል ማምረት | አንድ | አንድ | - | አንድ ( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | ሁለት | አንድ | - | ሁለት ( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |

| ፊ.ተራ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| | 16.ለስላሳ መጠጥ ማምረት፣ | - | አንድ | - | አንድ ( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | አንድ | አንድ | - | አንድ ( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| ሐ | <u>የጨርቃጨርቅና የጨርቃጨርቅ ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u><br>17.የጨርቃጨርቅ ፈትል ማምረት እና/ወይም ማቅለም<br>18.የተሸመነ ጨርቅ ማምረት እና/ወይም በመጨረሻ ደረጃ ጨርቅ ማዘጋጀት<br>19.ሹራብ ወይም ፎጣ ማምረት<br>20.አልባሳት ማምረት<br>21..የጨርቃጨርቅ ውጤቶች ተጓዳኝ አካላትን (accessories) ማምረት | አንድ (በተራ ቁጥር 17 እና 18 ለተመለከቱት ብቻ) | አንድ | - | አንድ ( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | ሁለት (በተራ ቁጥር 17 እና 18 ለተመለከቱት ብቻ) | አንድ | - | ሁለት ( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | ሁለት |
| | 22.ሌሎች ጨርቃጨርቆችን (ምንጣፍ፣የእግር መጥረጊያ፣ ወዘተ.)ማምረት | - | አንድ | - | አንድ ( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | አንድ | - | አንድ ( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |

| ተ.ቁ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| መ | **<u>የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u>**<br>23.የተቀናጀ የቆዳ ማልፋት ሥራ ( የክረስት ወይም ያለቀለት ቆዳ ደረጃን ጨምሮ)<br>24.በክረስት እና/ወይም በመጨረሻ ደረጃ ቆዳ ማልፋት<br>25.የቆዳ ውጤቶችን ማምረት<br>26.የቆዳ ውጤቶች ተጓዳኝ አካላትን (accessories) ማምረት | **አንድ**<br>(በተራ ቁጥር 23 እና 24 ለተመለከቱት ብቻ) | **አንድ**<br>(በተራ ቁጥር 25 እና 26 ለተመለከቱት ብቻ) | - | **አንድ**<br>( በሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **አንድ** | **ሁለት**<br>(በተራ ቁጥር 23 እና 24 ለተመለከቱት ብቻ) | **አንድ**<br>(በተራ ጥር 25 እና 26 ለተመለከቱት ብቻ) | - | **ሁለት**<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **ሁለት** |
| ሠ | **የእንጨት ውጤቶችን (እንጨት መሰንጠቅ እና ጣውላ ማምረትን ሳይጨምር) ማምረት** | - | - | - | **አንድ**<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **አንድ** | **አንድ** | - | - | **አንድ**<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **አንድ** |
| ረ | **<u>የፐልኘ፣ የወረቅትና የወረቀት ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u>**<br>27.ፐልኘ ማምረት<br>28.ወረቀት ማምረት | **አንድ**<br>(በተራ ቁጥር 27 ለተመለተከው ብቻ) | **አንድ**<br>(በተራ ቁጥር 28 ለተ መለ ተከው ብቻ) | - | **አንድ**<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **አንድ** | **ሁለት**<br>(በተራ ቁጥር 27 ለተመለከተው ብቻ) | **አንድ**<br>(በተራ ቁጥር 28 ለተ ለከተው ብቻ) | - | **ሁለት**<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **ሁለት** |

| ፊ.ተ.ራ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| | 29.የወረቀት ውጤቶችን ማምረት | - | አንድ | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | ሁለት | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| ሰ | የማተሚያ ኢንዱስትሪ አገልግሎት | - | አንድ | - | አንድ<br>(በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | ሁለት | - | አንድ<br>(በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| ሸ | ነዳጅ ማውጣትን ሳይጨምር ነዳጅ ማጣራት እና/ወይም የነዳጅ ውጤቶችን ማምረት | - | - | - | አንድ<br>(በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | - | - | አንድ<br>(በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | ሁለት |

| ፊ.ተ.ራ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| ቀ | <u>የኬማካልና የኬሚካል ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u><br>30.መሠረታዊ ኬሚካሎችን ማምረት<br>31.ማዳበሪያ እና/ወይም የናይትሮጅን ውህዶችን ማምረት | አንድ | - | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | ሁለት | - | - | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | ሁለት |
| | 32.የኘላስቲክ እና/ወይም ሠው ሠራሽ የጎማ ጥሬ ዕቃዎችን ማምረት | - | - | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | - | - | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| | 33.ፀረ-ተባይ፣ ፀረ-አረም ወይም ፀረ-ሺጋታ ማምረት | - | - | - | አንድ<br>(በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | አንድ | - | ሁለት<br>(በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |

| ፊ.ተራ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| | 34.የግድግዳ ቀለም፣ ቫርኒሽ ወይም መሰል መለሰኛዎችን፤ የማተሚያ፣ የመጻፊያ ወይም የሥዕል ቀለም ወይም ማጣበቂያ ማምረት<br>35.ሳሙና እና/ወይም መሰል የጽዳት ምርቶችን ማምረት<br>36.ሰው ሠራሽ ጭረቶችን ማምረት | - | አንድ | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | ሁለት | - | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| | 37.ሌሎች የኬሚካል ውጤቶችን(ባሩድ፣ፈንጂ፣የፎቶግራፍ ፊልም፣ ወዘተ.) ማምረት | - | አንድ | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | አንድ | - | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| በ | <u>የመሠረታዊ መድሓኒት ምርት እና የመድሓኒት ዝግጅት ኢንዱስትሪ</u><br>38.መሠረታዊ የመድኃኒት ግብዓቶችን ማምረት<br>39.መድሓኒት ማምረት/ማዘጋጀት | - | አንድ | አንድ | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | አንድ | አንድ | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | ሁለት |

| ፊ.ተ.ራ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| ተ | <u>ጎማና የፕላስቲክ ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u><br>40.የጎማ ውጤቶችን ማምረት | አንድ | - | - | አንድ<br><br>(በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | ሁለት | - | - | ሁለት<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| | 41.<u>የፕላስቲክ ውጤቶችን ማምረት</u><br>41.1 ለሕንጻ ግንባታ፣ ለተሽከሪካሪና ለሌሎች የኢንዱስትሪ ምርቶች ግብዓት የሚሆኑ፤ ለመስኖና ለመጠጥ ውሃ ማስተላለፊያነት እንዲሁም ለፍሳሽ ማስወገጃ የሚያገለግሉ የፕላስትክ ቧንቧዎችን/ቱቦዎችን እና መገጣጠሚያዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | - | አንድ<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ) | አንድ | አንድ | አንድ | - | ሁለት<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ) | አንድ |
| | 41.2 ሌሎች የፕላስቲክ ውጤቶችን ማምረት | - | አንድ | - | አንድ<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ) | አንድ | - | አንድ | - | ሁለት<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ) | አንድ |

| ፊ.ተራ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| ቸ | **<u>ብረት ያልሆኑ(non-metalllic) ሌሎች ማዕድን ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u>**<br>42 መስተዋት እና/ ወይም የመስታወት ውጤቶችን ማምረት<br>43 የሴራሚክ ውጤቶችን ማምረት<br>44 ሲሚንቶ ማምረት | **አንድ** | - | - | **አንድ**<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ) | **አንድ** | **ሁለት** | - | - | **ሁለት**<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ) | **አንድ** |
| | 45 ኖራ፣ ጀሶ እና/ወይም የመሳሰሉ መለሰኛዎችን ማምረት<br>46 የወፍጮ ድንጋይ፣ የብርጭቆ ወረቀት ወይም የድምጽ መገደብያ ወይም የሙቀት መከላከያ ምርቶችን ማምረት | **አንድ**<br>(የብርጭቆ ወረቀት ወይም የድምጽ መገደብያ ወይም የሙቀት መከላከያ ምርቶችን ሳይጨምር) | - | - | **አንድ**<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **አንድ** | **ሁለት**<br>(የብርጭቆ ወረቀት ወይም የድምጽ መገደብያ ወይም የሙቀት መከላከያ ምርቶችን ሳይጨምር) | - | - | **ሁለት**<br>( በ ሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **አንድ** |

| ፊ.ተራ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| ኀ | **<u>የመሠረታዊ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ[1]</u>**<br>47 መሠረታዊ ብረትና የአረብ ብረት ማምረት<br>48 መሠረታዊ የከበሩና የብረት ይዘት የሌላቸው ብረታ ብረቶችን (ሽቦ፤የመዳብ፣የብር፣የክሮም፣ ወዘተ. ቅልቅሎች፣ መጠቅለያ፣ ወዘተ.) ማምረት<br>49 ከብረት እና ከአረብ ብረት ፈሳሽ የተለያዩ ቅርጾችን ማውጣት | አንድ | - | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | ሁለት | - | - | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| ነ | **<u>የማምረቻ መሣሪያዎችንና ዕቃዎችን ማምረት የማይጨምር የብረታብረት ዕቃዎች ኢንዱስትሪ</u>**<br>50 የማዋቀሪያ ብረት ውጤቶችን፣ በርሜሎችን፣ ገንዳዎችን ወይም የእንፋሎት ማመንጫዎችን ማምረት | አንድ | - | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | ሁለት | - | - | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |

[1] ማዕድኑን ማውጣትን ሳይጨምር

| ተ.ቁ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| | 51 የጦር መሣሪያዎችን፣ ጥይቶችን ወይም ፈንጂዎችን ማምረት | - | - | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | አንድ | - | - | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| | 52 ሌሎች የብረታ ብረት ውጤቶችን(የእጅ መሣሪያ፣ ቁሳቁስ፣ ምስማር፣ ወዘተ.) ማምረት | - | - | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | አንድ | - | - | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| ኘ | <u>የኮምፒዩተር፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የዕይታ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ</u><br>53 የኤሌክትሮኒክስ አካሎችንና ሰሌዳዎችን ማምረት | - | አንድ | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | አንድ | - | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |

| ተ.ራ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| | 54 ኮምፒዩተር እና ተጓዳኝ ዕቃዎችን ማምረት<br>55 የመገናኛ መሣሪያዎችን ማምረት<br>56 የፍጆታ ኤሌክትሮኒክስ (ቴሌቪዥን፣ ዲ.ቪ.ዲ፣ሬድዮ፣ ወዘተ.) ዕቃዎችን ማምረት<br>57 የመለኪያ፣ የመፈተሻ፣ የመቃኛ፣ የመቆጣጠሪያ እና/ወይም ሰዓት ማምረት<br>58 የሕክምና መሣሪያዎችን (irradiation፣ electro-medical ወይም electrotherapeutic) ማምረት<br>59 የዕይታ ወይም የፎቶ ማንሻ ዕቃዎችን ማምረት | - | - | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | - | - | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| አ | <u>**የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ**</u><br>60 የኤሌክትሪክ ሞተር፣ ጀነሬተር፣ ትራንስፎርመር ወይም የኤሌትሪክ ማከፋፈያ ወይም መቆጣጠሪያ ዕቃዎችን ማምረት | አንድ | - | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | አንድ | - | - | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |

| ፊ.ተ.ራ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| | 61 የኤሌክትሪክ ኃይል ማከማቻ ወይም ባትሪ ማምረት<br>62 የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎችን / ኬብሎችን እና ተያያዥ ዕቃዎችን ማምረት<br>63 የኤሌክትሪክ ብርሃን መስጫ ዕቃዎችን ማምረት<br>64 የቤት ውስጥ መገልገያ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን ማምረት<br>65 ሌሎች የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን (አቀጣጣይ፣ ዲናሞ፣ አደጋ አመልካች፣ ወዘተ.) ማምረት | - | አንድ | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | አንድ | - | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| ከ | <u>ማምረቻ/አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎችና ዕቃዎች ኢንዱስትሪ</u><br>66 ሁለገብ መሣሪያዎችን (ሞተር፣ ዕቃ ማንሻ፣ ፐምፕ፣ ወዘተ.) ማምረት<br>67 ለተለያዩ ዓላማዎች የሚውሉ መሣሪያዎችን (የግብርና፣ ቆዳማልፊያ፣የጨርቃጨርቅ፣ወዘተ.) ማምረት | አንድ | - | - | አንድ<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | አንድ | - | - | ሁለት<br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |

| ፊ.ተራ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| ኸ | <u>**የመኪና፣የተጎታች እና ከፊል ተጎታች ኢንዱስትሪ**</u><br><br>68 አካላትን በመገጣጠም መኪና ማምረት | - | - | - | አንድ<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | - | - | ሁለት<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |
| | 69. የመኪና አካላትን& ተጎታችን እና/ወይም ከፊል ተጎታችን ማምረት | አንድ | - | - | አንድ<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | አንድ | - | - | ሁለት<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ | አንድ |
| | 70. የመኪና መለዋወጫዎችን እና ተጓዳኝ አካላትን (accessories) ማምረት | - | አንድ- | - | አንድ<br><br>(በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ | - | አንድ | - | ሁለት<br><br>(በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | አንድ |

| ፊ.ተ ራ | የማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስኮች | የልማት አካባቢ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20 ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች | | | | | ሌሎች አካባቢዎች | | | | |
| | | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ | የጭነት መኪና | ዴሊቨሪ ቫን | ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪና | ጀልባ | ፒክ አፕ |
| | 71. ሌሎች የትራንስፖርት ዕቃዎችን (ጀልባ፣ ብስክሌት፣ ሞተር ብስክሌት፣ ወዘተ.) ማምረት/መገጣጠም | - | - | - | **አንድ**<br><br>( በፕሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **አንድ** | - | - | - | **ሁለት**<br>( በፕ ሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **አንድ** |
| **ወ** | **የቢሮና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን (ከሴራሚክ የሚሠሩትን ሳይጨምር) ማምረት** | - | - | - | **አንድ**<br><br>( በፕ ሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **አንድ** | - | - | - | **ሁለት**<br>( በፕ ሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **አንድ** |
| **ዐ** | **ሌሎች ዕቃዎችን (የጌጣጌጥና ተዛማጅ ሥራዎች፣ የሙዚቃ መሣሪያዎች፣ የስፖርት ዕቃዎች፣ መጫወቻዎችና አሻንጉሊቶች፣ የሕክምና መሣሪያዎች፣ ወዘተ.) ማምረት** | - | - | - | **አንድ**<br><br>( በፕ ሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **አንድ** | - | - | - | **ሁለት**<br><br>( በፕ ሮጀክቱ አካባቢ ሐይቅ ወይም ወንዝ በመኖሩ ወደ ፕሮጀክቱ ለመመላለስ ጀልባ የሚያስፈልግ ከሆነ ) | **አንድ** |

4) በዚህ መመሪያ በአባሪው ከተመለከቱት በስተቀር በደንብ ቁጥር 84/1995 (እንደተሻሻለ) ከተዘረዘሩት የማምረቻ ኢንዱስትሪ የኢንቨስትመንት መስኮች መካከል በአንዱ ለሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀደው ባለሀብቱ፡-

ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ (የፋብሪካ ሕንፃ ተከራይቶም ከሆነ ሕጋዊ የኪራይ ውል) ማስረጃ፣

ለ/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት ፣ መሠረተ ልማት፣ መጋዘን፣ መንገድ እና የመሣሠሉት ሥራዎች እየተከናወኑ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ካለበት የኢንቨስትመንት መ/ቤት የተሰጠውን ማስረጃ፣

ሐ/ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Airway Bill) ወይም ትራክዌይ ቢል (Truck way Bill) እና የግዢ ደረሰኝ (Invoice) ወይም የካፒታል ዕቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግዢውን ውል ከአስፈላጊ ማስረጃዎች ጋር፣

መ/ ባለሀብቱ የፋብሪካ ሕንፃ ተከራይቶ የሚሠራ ከሆነ የመሣሪያ ተከላ ስለመጀመሩ ፕሮጀክቱ ካለበት የኢንቨስትመንት መ/ቤት የተሰጠውን ማስረጃ፣ እና

ሠ/ በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሠነድ እና/ወይም በራስ ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ በባንክ አካውንቱ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልፅ ወቅታዊ የባንክ እስቴትመንት፣

የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ከፊደል ተራ 'ሀ' እስከ 'ሠ' የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ባለሀብት ከፒክ-አፕ በስተቀር ሌሎቹን ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ለማስገባት የሚፈቀድለት የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የሙከራ ምርት ማምረት ስለመጀመሩ አግባብ ካለው አካል የተሰጠውን ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

6) ባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የማምረት ሥራ ሲጀምር ኢንቨስት ያደረገው የካፒታል መጠን በዚህ መመሪያ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 በተመለከተው መሠረት የተሟላ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣበት አካል የተሰጠውን ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለፈቀደው አካል ማቅረብ ያለበት ሲሆን፣ የካፒታል መጠኑ ከተመለከተው በታች ሆኖ ከተገኘ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ላስገባው/ቸው ተሽከርካሪ/ዎች ተገቢውን የጉምሩክ ቀረጥ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 5

## ለግብርና ኢንቨስትመንት መስኮች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1) በግብርና ሥራ መስክ የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 እና 6 በተገለፀው መሠረት በሚያለማው የመሬት ስፋት፤ በሚኖረው የእንስሣት ብዛት፣ የቀፎ ብዛት ወይም የሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት ነው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሀብቱ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት፣

   ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ ወይም ተከራይቶም ከሆነ የኪራይ ውል ማስረጃ፣

   ለ/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት፣ መሠረተ ልማት ፣ መጋዘን፣ መንገድ እና የመሣሠሉት ሥራዎች እየተከናወኑ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት ክልል የኢንቨስትመንት መ/ቤት የተሰጠው ማስረጃ፣ እና

   ሐ/ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Airway Bill) ወይም ትራክዌይ ቢል (Truck way Bill) እና የግዢ ደረሰኝ (Invoice)፣ ወይም

   መ/ የካፒታል ዕቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግዢውን ውል ከአስፈላጊ ማስረጃዎች ጋር፣

የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል ተራ ‘ሀ’ እስከ ‘መ‘ የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ባለሀብት ከፒክ-አፕ በስተቀር ሌሎቹን ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ለማስገባት የሚፈቀድለት የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የሙከራ ምርት ማምረት ስለመጀመሩ አግባብ ካለው አካል የተሰጠውን ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

4) ባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የማምረት ሥራ ሲጀምር ያለማው የመሬት ስፋት ወይም ያለው የእንስሳት ብዛት ወይም የቀፎ ብዛት ወይም የሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 እና 6 የተመለከተው መጠን የተሟላ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣበት አካል የተሰጠውን ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለፈቀደው አካል ማቅረብ ያለበት ሲሆን፣ መጠኑ ከተመለከተው በታች ሆኖ ከተገኘ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ላስገባው/ቸው ተሽከርካሪ/ዎች ተገቢውን የጉምሩክ ቀረጥ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

5) ለእርሻ ልማት ኢንቨስትመንት ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀደው ከዚህ በታች በተገለፀው ሠንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

| ፊ. ተ ራ | የእርሻ ኢንቨስትመንት መስክ | የሚለማው የመሬት መጠን (ሄክታር) | የአስተዳደር አካባቢዎች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | አዲስ አበባ፣በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ እስከ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች (ለ) | ሌሎች አካባቢዎች (መ) |
| ሀ) | **<u>ቋሚ ያልሆኑ ሰብሎች ልማት</u>**<br>1. የብርዕ፣ የአገዳ፣ የጥራጥሬ እና/ወይም የቅባት እህሎችን ማምረት | ከ200 - 300 | — | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ300 በላይ | — | 1 ፒክ አፕ<br>2 ሞተር ብስክሌት |
| | 2. አትክልት እና/ወይም የምግብ ሥራ ሥሮችን ማምረት | ከ50 - 100 | 1 ፒክ አፕ<br>1 ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነትመኪና | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>1 ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪና |
| | | ከ100 በላይ | 2 ፒክ አፕ<br>2 ማቀዝቀዣየተገጠመለት የጭነት መኪና | 2 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>2 ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪና |
| | 3. የሸንኮራ አገዳ እና/ወይም የስኳር ሥራሥሮችን ማምረት | ከ500 በላይ | — | 2 ፒክ አፕ<br>2 ሞተር ብስክሌት<br>2 የጭነት መኪና |
| | 4. የትንባሆ ቅጠል ማምረት | ከ50 በላይ | — | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | 5. የጭረት ሰብሎችን ማምረት | ከ200 - 300 | — | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>1 የጭነት መኪና |
| | | ከ300 በላይ | — | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>2 የጭነት መኪና |
| | 6. ለእንስሳትመኖነት፣ | ከ200 በላይ | — | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>1 የጭነት መኪና |
| | 7. የተረጋገጠ ምርጥ ዘር ማምረት | ከ50 በላይ | — | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>1 የጭነት መኪና |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 8. ሌሎች ቋሚ ያልሆኑ የግብርና ምርቶችን ( አበባ፤ ለመድሀኒት፣ ለሽቶ፣ ለቅመምነት፣ ወዘተ. የሚሆኑ) ማምረት | ከ10 - 30 | 1 ፒክ አፕ<br>1 ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪና (ለአበባ ብቻ) | 1 ፒክ አፕ<br>1 ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪና (ለአበባ ብቻ) |
| | | ከ30 በላይ | 1 ፒክ አፕ<br>1 ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪና (ለአበባ ብቻ) | 1 ፒክ<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>1 ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪና (ለአበባ ብቻ) |
| ለ) | <u>የቋሚ ተክሎች ልማት</u><br>9. የወይን ተክል ልማት<br>10. የሌሎች ፍራፍሬ ልማት | ከ50 - 100 | 1 ፒክ አፕ<br>1 ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪና | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>1 ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪና |
| | | ከ100 በላይ | 2 ፒክ አፕ<br>2 ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪና | 2 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>2 ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪና |
| | 11. የመጠጥ ተክል (ቡና፣ ሻይና ሌሎች) ልማት | ከ150 - 300 | — | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት<br>1 የጭነት መኪና |
| | | ከ300 በላይ | — | 1 ፒክ አፕ<br>2 ሞተር ብስክሌቶች<br>1 የጭነት መኪና |
| | 12. የቅመማ ቅመም፣ የመዓዛ እና/ወይም የመድሐኒት ተክል ልማት | ከ50-100 | — | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| | | ከ100 በላይ | — | 1 ፒክ አፕ<br>2 ሞተር ብስክሌት |
| | 13. የሌሎች ቋሚ ተክሎች (የጎማ ዛፍ፣ ጉሎ፣ ጃትሮፋ፣ ፓልም፣ ወዘተ.) ልማት | ከ300 - 500 | — | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌቶች |
| | 14. የደን ልማት | ከ500 በላይ | — | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌቶች<br>1 ቶም ካር |

6) ለእንሰሳት ሀብት ልማት ኢንቨስትመንት ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀደው ከዚህ በታች በተገለፀው ሠንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

| ተ.ቀ. | የእንስሳት ሀብት ልማት ኢንቨስትመንት መስክ | የፕሮጀክት አቅም በእንሰሳት ብዛት ፣ በቀፎ ብዛት ወይም በሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት | የአስተዳደር አካባቢዎች | |
|---|---|---|---|---|
| | | | አዲስ አበባ፣በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን እና ከልዩ ዞኑ እስከ አዳማ (አዳማን ጨምሮ) ባለው ዋና መንገድ እስከ 20ኪ.ሜ ግራና ቀኝ ያሉ አካባቢዎች (ለ) | ሌሎች አካባቢዎች (መ) |
| 1. | የቤት እንስሳት እርባታ፣ ማደለብ እና ተዋጽኦ ልማት | ከ250-500 እንስሳት | 1 ፒክ አፕ | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| 2. | የዱር እንስሳት እርባታ እና ተዋጽኦ ልማት | ከ500 እንስሳት በላይ | 1 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት | 2 ፒክ አፕ<br>1 ሞተር ብስክሌት |
| 3. | ንብ ማነብ እና ማር ማምረት | ከ500-1000 ቀፎ | 1 ፒክ አፕ | 1 ፒክ አፕ |
| | | ከ1000 ቀፎ በላይ | 1 ፒክ አፕ | 2 ፒክ አፕ |
| 4. | በሰው ሰራሽ ኩሬ አሳ ማምረት | ከ1250ሜ.ኩ-2000 ሜ.ኩ | 1 ፒክ አፕ | 1 ፒክ አፕ |
| | | ከ2000 ሜ.ኩ በላይ | 1 ፒክ አፕ | 2 ፒክ አፕ |

## አንቀጽ 6

## ለኮንስትራክሽን፣ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ ለምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ግንባታ ሥራ ተቋራጭነቶች እንዲሁም ለልዩ ሥራ ተቋራጭነት የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1) በኮንስትራክሽን፣ በውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ በምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮና ግንባታ ሥራ ተቋራጭነቶች ወይም በልዩ ሥራ ተቋራጭነት የተሠማራ ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በተገለፀው መሠረት ነው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከቱት የሥራ መስኮች የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ባለሀብቱ፡-

ሀ/ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለደረጃው እንደሚያስፈልጉ ከዘረዘራቸው መሣሪያዎች በዋጋ ሃያ አምስት በመቶ (25%) ያህሉን ከውጭ

ሀገር ስለመግዛቱ ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Airway Bill) ወይም ትራክዌይ ቢል (Truck way Bill) እና የግዢ ደረሰኝ (Invoice) ወይም ሌላ የዋጋ ግምት ማረጋገጫ ሠነድ ፣ ወይም

ለ/ መሣሪያዎቹን ከሀገር ውስጥ የገዛ ከሆነ የግዢ ውሉን ከአስፈላጊ ሠነዶች ጋር፣

የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

3) ለውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ለመሠረት ጉድጓድ ቁፋሮና ግንባታ ሥራ ተቋራጭነት የኢንቨስትመንት መስኮች ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀደው ድሪሊንግ ሪጉ ወይም ጉድጓድ መቆፈሪያው/መሠርሠሪያው የተገዛ ስለመሆኑ ማረጋገጫ፣ የማስጫኛ ሠነድ እና ሪጉ ወይም መቆፈሪያው/መሠርሠሪያው ወደ አገር ውስጥ ስለመግባቱ ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

4) ለኮንስትራክሽን፣ ለውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ ለምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮና ግንባታ ሥራ ተቋራጭነቶች ወይም ለልዩ ሥራ ተቋራጭነት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የሚፈቀዱ የተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት የሚወሰነው ከዚህ በታች በተገለፀው ሠንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

| ተራ ቁጥር | የኮንስትራክሽን ዘርፍ | ደረጃ አንድ | ደረጃ ሁለት | ደረጃ ሦስት | ደረጃ አራት | ደረጃ አምስት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭነት | | | | | |
| | - ፒክ አፕ | 7 | 6 | 4 | 3 | 1 |
| 2 | የሕንፃ ሥራ ተቋራጭነት | | | | | |
| | - ፒክ አፕ | 4 | 3 | 2 | 2 | 1 |
| | - የጭነት መኪና | 2 | 1 | - | - | - |
| 3 | የመንገድ ሥራ ተቋራጭነት | | | | | |
| | - ፒክ አፕ | 6 | 5 | 3 | 2 | - |
| 4 | ልዩ ሥራ ተቋራጭነት (ለኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራ ብቻ) | | | | | |
| | - ፒክ አፕ | 3 | 2 | - | - | - |
| | - የጭነት መኪና | 2 | 2 | - | - | - |
| 5 | የምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮና ግንባታ ሥራ ተቋራጭነት | ለአንድ መቆፈሪያ/መሰርሰሪያ መሣሪያ 2 ፒክ አፕ እና 1 ክሬን ትራክ፣ ሆኖም የሚፈቀደው ፒክ አፕ ብዛት ከ4 መብለጥ የለበትም፡፡ | | | | |
| 6 | የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ተቋ ራጭነት | ለአንድ ድሪሊንግ ሪግ 2 ፒክ አፕ እና 1 ክሬን ትራክ፣ ሆኖም የሚፈቀደው ፒክ አፕ ብዛት ከ4 መብለጥ የለበትም፡፡ | | | | |

## አንቀጽ 7

## የኮከብ ደረጃ ላላቸው የሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ)፣ የሞቴል፣ የሬስቶራንትና የሎጅ አገልግሎት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1) የኮከብ ደረጃ ያለው ሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ)፣ ሞቴል፣ ሬስቶራንት ወይም ሎጅ ለሚያቋቁም ማንኛውም ባለሀብት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በሚያወጣው የደረጃ መስፈርት መሠረት ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሠንጠረዥ አኳኋን ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ በነፃ ማስገባት ይችላል፡፡

| *የኮከብ ደረጃ* | *የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት* |
|---|---|
| 1 ወይም 2 | 1 ፒክ አፕ |
| 3 ወይም በላይ | 2 ፒክ አፕ |

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገባ በባለሀብት ሲጠየቅ፦

ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ ማስረጃ፣ እና

ለ/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የሕንፃው ግንባታ፣ መሠረተ ልማት እና መጋዘን የመሣሰሉት እየተሠሩ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት የኢንቨስትመንት መ/ቤት ማስረጃ

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 8

## ለመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ (ICT) ልማት ኢንቨስትመንት መስክ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

በኢንቨስትመንት ቦርድ በወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2001 መሠረት ማበረታቻ የሚፈቀድለት ማንኛውም በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት ኢንቨስትመንት መስክ የተሠማራ ባለሀብት ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

| የቋሚ ሠራተኞች ብዛት | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|
| 50 | 1 አውቶቡስ ወይም 2 ሚኒባስ እና<br>1 ዴሊቨሪ ቫን |
| ከ50 በላይ - 100 | 2 አውቶቡስ ወይም 3 ሚኒባስ እና 1 ዴሊቨሪ ቫን |
| ከ100 በላይ | 3 አውቶቡስ ወይም 4 ሚኒባስ እና<br>2 ዴሊቨሪ ቫን |

## አንቀጽ 9

## ለአስጎብኝነት ኢንቨስትመንት መስክ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1) በአስጎብኝነት ኢንቨስትመንት መስክ የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት 3 /ሦስት/ አዳዲስ ስቴሽን ዋገን ተሽከርካሪዎችን በአንድ ዓመት ውስጥ በሁለት ጊዜ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ተሽከርካሪዎቹን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀደው ባለሀብቱ፡-

   ሀ/ የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ያወጣውን መስፈርት በማሟላት አግባብ ካለው አካል የማስጎብኘት አገልግሎት ፈቃድ አውጥቶ/አግኝቶ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ወይም ወደ ኢንቨስትመንት መስኩ የሚሠማራ መሆን ይኖርበታል፡፡

   ለ/ ተሽከርካሪዎቹ አዳዲስ ስለመሆናቸው ከተፈበረኩበት/ባቸው ፋብሪካ/ዎች ወይም ከአቅራቢዎች ማስረጃ ማቅረብ፣ ለማስጎብኘት ሥራ ብቻ እንዲያውላቸው ግዴታ መግባትና የመተማመኛ ግዴታ ሠነዱንም በባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ፊት ቀርቦ መፈረም እና ይኸውም በሚኒስቴሩ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ለአስጎብኝነት ሥራ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን ለመለየት በባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በሚወሰነው መሠረት የመለያ ምልክት እንዲኖራቸው ይደረጋል፤ ተሽከርካሪዎቹ ለተፈቀደላቸው ዓላማ መዋላቸውንም እንዲቆጣጠርና እንዲያረጋግጥ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## አንቀጽ 10

## ለኢንዱስትሪ ዞን ግንባታ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

በኢንዱስትሪ ዞን ግንባታ የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት 3 ፒክ አፕ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል፡፡

## አንቀጽ 11

## የሠራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች

1) በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ (ICT) ልማት እና በአስጎብኝነት ኢንቨስትመንት መስኮች ላይ የሚሰማሩትን ሳይጨምር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 ለተመለከቱት የኢንቨስትመንት መስኮች እና በደንቡ መሠረት ማበረታቻ ለሚፈቀድለት ማንኛውም ባለሀብት ለሠራተኛ ማጓጓዣ የሚያስፈልገውን ተሽከርካሪ እንደ ፕሮጀክቱ የሠራተኛ ብዛት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ በተመለከተው መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሠራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀደው ባለሀብቱ በቅድሚያ፣

ሀ/ መሬት ስለማግኘቱ/ተከራይቶም ከሆነ የኪራይ ውል ማስረጃ፣

ለ/ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Lading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Airway Bill) ወይም ትራክዌይ ቢል (Track-way Bill) እና የግዢ ደረሰኝ (Invoice)፣ ወይም

ሐ/ የካፒታል ዕቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግዢ ውል ከአስፈላጊ ሠነዶች ጋር፣

መ/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት፣ የሕንፃ ግንባታ፣ መሠረተ ልማት፣ መጋዘን እና መንገድ የመሣሰሉት እየተሠሩ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት የክልል ኢንቨስትመንት መ/ቤት ማስረጃ፣ እና

ሠ/ ለፕሮጀክቱ በቋሚነት ተቀጥረው በመሥራት ላይ የሚገኙ ሠራተኞችን ሥም ዝርዝር የያዘ ቢያንስ የሦስት ወር የደመወዝ መክፈያ ሠነድ (Pay-roll) እና ለመንግሥት የደመወዝ ግብር የተከፈለበት ማስረጃ

የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቀድው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሠራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ የሚፈቀደው ከዚህ በታች በተገለፀው ሠንጠረዥ መሠረት ነው፡፡

| ቋሚ የሠራተኛ ብዛት | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|
| ከ25 - 50 | 2 ሚኒባስ ወይም 1 አውቶቡስ |
| ከ50 በላይ | 3 ሚኒባስ ወይም 2 አውቶቡስ |

## ክፍል III

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 12

### በአገር ውስጥ ስለሚገጣጠሙ/ስለሚመረቱ ተሽከርካሪዎች

ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ባለሀብት ከአገር ውስጥ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ/ማምረቻ ፋብሪካ ተሽከርካሪ ሲገዛ ተሽከርካሪውን ለማምረት ከውጭ ተገዝተው በገቡ የተሽከርካሪው ግብዓቶች ላይ የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ ተሠልቶ ይቀነስለታል፡፡

### አንቀጽ 13

### የማስፋፊያ/የማሻሻያ ኢንቨስትመንቶች

በዚህ መመሪያ በአባሪው ከተመለከቱት በስተቀር በአንቀፅ 3 ከተዘረዘሩት ኢንቨስትመንት መስኮች መካከል በአንዱ የተሠማራ እና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994 (እንደተሸሻለ) መሠረት ነባር ድርጅቱን ያስፋፋ/ያሻሻለ ባለሀብት ለማስፋፊያ/ለማሻሻያ ፕሮጀክቱ በአንቀጽ 4፣5፣10 እና 11 ከተመለከቱት የተሽከሪካሪ ዓይነቶች አንዳንድ ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

## አንቀጽ 14

## የተሻሩ መመሪያዎች እና አንቀፅ

1) ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እንደገና ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 2/1999 ዓ.ም. ፣

2) በአስጎብኝነት የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ የተሠማሩ ባለሀብቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የሚያስገቧቸውን ተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2000 ዓ.ም. እና

3) በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት የኢንቨስትመንት መስክ ከገቢ ግብርና ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመሆን ማበረታቻ የሚሰጥባቸው የሥራ መስኮችና ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የሚገቡ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን ዓይነት ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2001 ዓ.ም. አንቀፅ 5 በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## አንቀጽ 15

## መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ የተሽከርካሪ ማበረታቻ መመሪያ እንዳስፈላጊነቱ በየጊዜው ሊሻሻል ይችላል፡፡

ይህ መመሪያ ከየካቲት 18 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል

አዲስ አበባ

-----------------------------

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ሰብሳቢ

# አባሪ

## የተሽከርካሪ ማበረታቻ የማይፈቀድላቸው የማምረቻ ኢንዱስትሪ ሥራ መስኮች

1. ዱቄት፣ ዳቦ፣ ኬክ እና/ወይም አይስ ክሬም ማምረት፣
2. ተበጥብጦ የሚታሸግ ጁስ ማምረት፣
3. የትንባሆ ውጤቶችን ማምረት፣
4. ጣውላ እና/ወይም ሞራሌ ማምረት፣
5. የቤት ክዳን ቆርቆሮ ወይም ምስማር ማምረት፣
6. የአስቤስቶስ ውጤቶችን ማምረት፣
7. ጠጠር ወይም ብሎኬት ማምረት፣
8. የሚዲያ ውጤቶችን ማምረት ወይም ማባዛት፣